የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት
ጄኔቫ

# ሞዴል የውክልና ሥልጣን

ቀን ___ ወር _____ 19 ___ ዓ.ም.

| | |
|---|---|
| ወካይ ፡ ____________________ | ተወካይ ፡ ____________________ |
| የመታወቂያ ቁ. / | |
| የፓስፖርት ቁ. ____________ | |
| ዜግነት ፡ ኢትዮጵያዊ/ት | ዜግነት ፡ ኢትዮጵያዊ/ት |
| አድራሻ (Switzerland) | አድራሻ (ኢትዮጵያ) |
| ____________________ | ክልል፡ ______ ወረዳ ፡ ______ |
| ____________________ | ቀበሌ፡ _____ የቤት ቁጥር፡ ______ |
| ስልክ ቁ. ____________________ | ስልክ ቁ. ____________________ |

እኔ ወካይ ለተወካዩ የምሰጣቸው ውክልና ተወካዩ እንደእኔ በመሆን በማንኛውም ማመልከቻ ላይ እየፈረሙና እያረጋገጡ አቤቱታ እንዲያቀርቡ፣ ወራሽነቴን በፍርድ ቤት እንዲያረጋግጡ፣ በውርስ የሚደርሰኝን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረትና ገንዘብ እንደ እኔ ሆነው እንዲረከቡና ድርሻዮን እንዲወስዱ፣ ክፍያ እንዲከፍሉ፣ እንዲሸጡ እንዲለውጡ፣ እንዲያስተዳድሩ በስሜ እንዲያዞሩ፣ ከመንግሥት በሊዝም ይሁን በምሪት በዜግነቴ የማገኘውን ለቤት መስሪያ የሚሆን ቦታ እንዲመሩ፣ የመኖሪያም ሆነ የንግድ ቤት እንዲሰሩ፣ እንዲያስተዳድሩ፣ ንብረቴን በዋስትና በማስያዝ ገንዘብ ከባንክም ሆነ ከግለሰብ እንዲበደሩ፣ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኝ የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረቴን እንደ እኔ በመሆን ለማስተዳደር፣ ለመጠበቅ፣ ለመቆጣጠር፣ ለመሸጥ ለመለወጥ ውል ለመዋዋል፣ ገንዘብ ለመቀበል፣ ስም ለማዛወር በስሜ የተመዘገበውን የባንክ ሂሳብ ለማንቀሳቀስ ገቢና ወጪ ለማድረግ እንዲችሉ፣ ቼክ እንዲቀበሉ እንዲመነዝሩና እንዲፈርሙ፣ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙና እንዲቀበሉ፣ በስሜ የተዘጋጁ ዶክሜንቶችን እንዲቀበሉ፣ ከውጭ አገር በስሜ ተመዝግቦ የሚመጣልኝን እቃ አስፈላጊውን የጉምሩክ ፎርማሊቲ አሟልተውና ቀረጡን ከፍለው እንዲረከቡ፣ ክርክር ቢነሳ የሕግ ጠበቃ ወክለው እንዲከራከሩ፣ መልስ እንዲሰጡ፣ ቃለ መሓላ እንዲያቀርቡ፣ አክስዮን እንዲገዙና እንዲሸጡ በንብረቴም ሆነ በማንኛውም ሌላ ጉዳይ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ውክልና እንዲሰጡ፣ በአጠቃላይ ተወካዬ በማናቸውም የአስተዳደር፣ በመንግሥታዊ፣ በህዝባዊ፣ በግል ድርጅቶችና መሥሪያ ቤቶች ተገኝተው እኔ መፈጸም እና ማከናወን የሚገባኝን ማናቸውንም ጉዳዮች ሁሉ ተከታትለው እንዲፈጽሙና እንዲያስፈጽሙ እኔ መሥራት የሚገባኝን ሥራዎች እንደ እኔ ሆነው እንዲሰሩ ስለ እኔ ተጠሪ እንዲሆኑ ስል ይህንን ሙሉ የውክልና ሥልጣን በፍ/ሕ/ቁ/ 2199 መሰረት የሰጠኋቸው መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ፊርማ፡ ____________________ የወካይ ስም፡ ____________________

ማስታወሻ:-

ይህ ሞዴል ውክልና መስጫ ለሁሉም ውክልና ላያገለግል እንደሚችልና ውክልና ሰጪው እንደ ጉዳዩ አይነት ይዘቱን መቀየር የሚችል መሆኑን እንገልጻለን።

*Consular Section*
56, Rue de Moillebeau
P. O. Box 338
1211 Geneva 19
Switzerland

Tel. (022) 919 70 16/10
Fax: (022) 919 70 29
E-mail: mission.ethiopia@ties.itu.int
http://www.ethiopianmission.ch/